አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ቢሮ

Addis Ababa City Administration
Public Service & Human Resource Development Bureau

ቁጥር ጽ/ም11-09/60/422 ቀን 30-10-2014
Ref. No Date

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
ለትምህርት ቢሮ
አዲስ አበባ

ጉዳዩ፡- **የኮንትራት የጤና ባለሙያዎች ጥያቄ ምላሽ ይመለከታል፤**

ቢሮአችን በቁጥር 08-ጠ11-09/53/339 በቀን 07/10/2014 በጻፈው ደብዳቤ የኮቪድ ወራርሽኝ ከፍተኛ ደረጃ በደረሰበት ወቅት የኢፌዲሪ ጤና ሚኒስቴር እና የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጤና ቢሮ ባወጡት የኮቪድ -19 መከላከያ ፕሮቶኮል ለመተግበር እና የመማር ማስተማሩን ስራ ለማስቀጠል ከ1800 በላይ የሚሆኑ የጤና ባለሙያዎች የኮንትራት ጊዜያቸው ከመጠናቀቁ በፊት ወደ ቋሚነት እንዲቀየሩ የፈቀድንላችሁ መሆኑ ይታወቃል፡፡

በመሆኑም እነዚህ የጤና ባለሙያዎች በኮቪድ 19-ወራርሽኝ ወቅት ያለውን ችግር በመጋፈጥ ተማሪዎችን እና የትምህርት ቤት ማህበረሰብን ሲረዱ የቆዩና አሁንም በመስራት ላይ የሚገኙ መሆናቸውን፣ በሀጋዊ መንገድ ተወዳድረው ፈተናውን በማለፍ በኮንትራት መቀጠራቸው፣ በስራ አፈፃፀም ብቁ መሆናቸው እና ከባለሙያዎቹ በስተጀርባ ያለውን ቤተሰብና የትምህርት ማህበረሰቡን መልካም አስተዳደር ጥያቄ ለመመለስ **የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ የሚያወጣውን መመዘኛ መስፈርት የሚያሟሉ ጤና ባለሙያዎችን** በቋሚ ቅጥር አፈፃፀም መመሪያን በመከተል በልዩ ሁኔታ ለአንድ ጊዜ ብቻ ጤና ባለሙያዎችን ወደ ቋሚነት ማዘዋወር እንድትችሉ የተፈቀደላችሁ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

ብሩ ዘውዴ (ዶ/ር)
በቢሮ ሀላፊ ደረጃ የሰው ሀብት ልማትና አስተዳደር ዘርፍ ኃላፊ

ግልባጭ

በፐብሊክ ሰርቪስና የሰዉ ሀብት ልማት ቢሮ

- በቢሮ ኃላፊ ደረጃ ለሰዉ ሀብት ልማትና አስተዳደር ዘርፍ
- ለሰዉ ሀብት ልማት ስምሪትና መረጃ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት

አዲስ አበባ